EDTF

ETHIOPIAN DIASPORA TRUST FUND

# የዜና እወጃ

## የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ የጊዜውን ወረርሽኝ ለመከላከል የሚረዳ ከብር 40 ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ የገዛቸውን የመጀመርያ ዙር የህክምና መርጃ ዕቃዎችን ለኢትዮጵያ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስረከበ።

**ግንቦት 28 ቀን 2012 ዓ.ም አዲስ አበባ**

በኢትዮጵያ የተከሰተውን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ለመዋጋት የታወጀውን ሀገራዊ ዘመቻ ተከትሎ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ከ 40 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ለህክምና የሚረዳ የቁሳቁስ ድጋፍ በዛሬው ዕለት ለኢትዮጵያ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በማስረከብ ወገናዊ አለኝታነቱን እና ፈጥኖ ደራሽነቱን አረጋገጠ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ያቋቋመው የኮቪድ-19 ልዮ ግብረ ኃይል በዚህ እጅግ ፈታኝ ወቅት ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ወገኖቻቸውን ለመታደግ በመላ ሀገሪቱ በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈው አገልግሎት በመስጠት ላይ ላሉ የጤና ባለሙያዎች ሥራቸውን ሲያከናውኑ ለበሽታው የበለጠ ተጋላጭ በመሆናቸው ሊደርስባቸው የሚችለውን ጥቃት ለመቀነስ ብሎም ለመታደግ የሚረዱ ልዩ ልዩ መሳርያዎችን ገዝቶ አስረከበ።

የጤና አጠባበቅ ሥርዓታችንን ለመደገፍ የሚያስችሉ አንድ ሚሊዮን በቀዶ ጥገና ጊዜ የሚያገለግሉ የፊት መሸፈኛ ጭምብሎች፣ 42 ሺህ መተንፈሻ የተገጠመላቸው የፊት መከላከያዎች፣ 19 ሺህ የመከላከያ አልባሳት፣ 10 ሺህ አፍንጫ ላይ የሚገጠሙ የመተንፈሻ መሣርያዎች፣ 2 ሺህ የፊት መከላከያ ሽፋኖች እና 420 የሙቀት መለክያዎችን በዛሬው ርክክብ ላይ የተካተቱ ሲሆን ማሌዥያ ውስጥ በመመረት ላይ ያለው 6.6 ሚሊዮን የህክምና የእጅ ጓንቶች የምርት ስራው እንደተጠናቀቀ የምናስረክብ ይሆናል።

የሰው ልጅ ሥጋት የሆነውን የኮረና ወረርሽኝ ፈተና በአንድነት ተጋግዘን በመከላከል የነገውን ብሩህ ተስፋ እንድንጨብጥ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከጤና ባለሙያዎች የሚሰጠውን ምክር እና መመርያ ተግባራዊ በማድረግ ከኮረና ቫይረስ ቤተሰቡን እና ማህበረሰቡን በመጠበቅ የመፍትሔው አካል እንዲሆን የኢትዮጵያ ዳይስፖራ ትረስት ፈንድ ጥሪውን እያቀረበ እስካሁን በቫይረሱ ለተያዙት እና በጊዝያዊ ማቆያ ለሚገኙት በሙሉ ፈጣሪ ምህረቱን እንዲሰጥልን እየተመኘ ትረስት ፈንዱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆሙን ይገልፃል።

በመላው ዓለም ካሉት ደጋፊዎቹ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ለማሰባሰብ አዲስ በከፈተው ልዩ መስኮት ተጠቅመው የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ወረርሽኙ ስር ሳይሰድ መከላከል እንዲቻል የበኩልዎን እንዲወጡ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ጥሪ ያቀርባል።






ለተጨማሪ መረጃ፡

ለሚዲያ ጥያቄ፡ **ሀና አጥናፉ** - የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ የኮምንኬሽን ስፔሻሊስት +251 955 332 933